ደንብ ቁጥር ---/፪ሺ፲፷

የካፒታል ገበያ የካሳ ፈንድ አስተዳደርን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የካፒታል ገበያ የካሳ ፈንድ ዝርዝር የፋይናንስ እና የአስተዳደር ጉዳዮችን በተመለከተ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ እንደሚወጣ በካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፵፰/፪ሺ፲፫ የተደነገገ በመሆኑ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፵፰/፪ሺ፲፫ አንቀጽ ፩፻፫ እና ፩፻፹ (፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የካፒታል ገበያ የካሳ ፈንድ ደንብ ቁጥር ___/፪ሺ___" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩/ "ባለሥልጣን" ማለት በአዋጁ አንቀጽ ፫ መሠረት የተቋቋመው የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ነው።

፪/ "ቦርድ" ማለት የባለሥልጣኑ ዳይሬክተሮች ቦርድ ነው።

፫/ "ፈንድ" ማለት በአዋጁ አንቀጽ ፩፻፫ መሠረት የተቋቋመው የካፒታል ገበያ ካሳ ፈንድ ነው።

፬/ "እስከ ሦስተኛ ደረጃ የሚቆጠሩ ዘመዶች" ማለት ወላጆችን፣ ልጆችን፣ የልጅ ልጆችን፣ ወንድሞች እና እህቶችን፣ አጎቶችን አክስቶችን፣ የወንድም ወይም የእህት ልጆችን፣ አያቶችን እና ቅድመ አያቶችን የሚያጠቃልል ዝምድና ነው።

፭/ "አዋጅ" ማለት የካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፵፰/፪ሺ፲፫ ነው።

፮/ ሌሎች በዚህ ደንብ ውስጥ የተጠቀሱ ቃላት እና ሐረጎች በአዋጁ ውስጥ የተሰጣቸውን ትርጓሜ ይይዛሉ።

፯/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተቀመጠ አገላለጽ ሁሉ የሴትንም ጾታ ይጨምራል፡፡

፫. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ ደንብ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚካሄዱ የካፒታል ገበያ ግብይቶች፣ ፈቃድ ያለው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ የውል ግዴታውን ባለመወጣቱ ምክንያት የገንዘብ ኪሣራ ለሚደርስባቸው ኢንቨስተሮች ካሣ ለመስጠት እና የመብት ጥያቄ ያልቀረበባቸውን የተሰበሰቡ የትርፍ ድርሻዎችን ሁኔታው ሲፈጠር ለተጠቃሚዎች ለመክፈል ተፈጻሚ ይሆናል።

ክፍል ሁለት

አስተዳደር እና የኢንቨስትመንት ፖሊሲ

፬. የፈንዱ አስተዳደር

፩/ ባለሥልጣኑ ፈንዱን የሚያስተዳድር ይሆናል።

፪/ ባለሥልጣኑ የካሳ ፈንድ አስተዳደር ኮሚቴ (ከዚህ በኋላ "ኮሚቴ" ተብሎ የሚጠራ) በቦርድ አጸድቆ ያቋቁማል።

Draft

፫/ ባለሥልጣኑ የኮሚቴውን አወቃቀር፣ ተግባር እና ኃላፊነቶች በመመሪያ ይወስናል።

፬/ የፈንዱ ሀብቶች ከባለሥልጣኑ አጠቃላይ ሀብቶች፣ እንዲሁም ከማንኛውም ሌሎች ፈንዶች ወይም ሂሳቦች ተለይተው መያዝ አለባቸው።

፭/ የፈንዱ ሀብቶች በዚህ ደንብ ውስጥ ለተመለከቱት ዓላማዎች ብቻ በባለሥልጣኑ በአደራ መያዝ ያለባቸው ሲሆን ከታለመላቸው ዓላማ ውጭ ለማንኛውም ሌላ ተግባር መዋል የለባቸውም።

፮/ የሚከተሉት ክፍያዎች ከፈንዱ ሊፈጸሙ ይችላሉ:-

> **ሀ/** ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ለኢንቨስተሮች የሚከፈል የካሳ ክፍያ፤
>
> **ለ/** ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የመብት ጥያቄ ያልቀረበባቸው የተሰበሰቡ የትርፍ ድርሻዎች ሁኔታው ሲፈጠር ለተጠቃሚዎች የሚከፈል ክፍያ፤
>
> **ሐ/** ፈንዱን ከማቋቋም፣ ከማስተዳደር እና ኢንቨስት ከማድረግ ጋር ለተያያዙ ማናቸውም ወጪዎች።

፯/ ከፈንዱ የሚከፈሉ ማናቸውም ክፍያዎች የሚፈጸሙት በኢትዮጵያ ብር ብቻ ነው።

፰/ ባለሥልጣኑ የፈንዱን ሀብቶች ለመጠበቅ፣ የካሳ ጥያቄዎችን ለማስተናገድና ለማስተዳደር፣ ከፈንዱ የሚከፈሉ ክፍያዎችን ለመወሰን ፣ ለፈንዱ የሚደረጉ መዋጮዎችን ለመወሰን፣ ለፈንዱ መመለስ የሚገባውን ገንዘብ ለማስመለስ የሚረዳ መረጃ ለሚሰጡ ግለሰቦች ሽልማት አሰጣጥን ጨምሮ የፈንዱን የዕለት ተዕለት ተግባራት ለማከናወን የሚጠቀምባቸውን ሂደቶችን በተመለከተ በመመሪያ ይወስናል።

፰. <u>የፈንዱ ገንዘብ ኢንቨስት የሚደረግበት ፖሊሲ</u>

፩/ ፈንዱ ግዴታውን መወጣት ያስችለው ዘንድ የካሳ ፈንዱ ሃብት የካፒታል ደህንነትን በመጠበቅ፣ ገንዘብ አከልነት እና ጥንቃቄ የታከለበት የስጋት ቁጥጥር መርሆዎችን መሠረት በማድረግ ኢንቨስት መደረግ አለበት።

፪/ ቦርዱ በየጊዜው በሚያጸድቀው መሰረት የፈንዱ ገንዘብ በባለሥልጣኑ አነስተኛ ስጋት አላቸው፣ ገንዘብ አከል እንዲሁም ብዝሃነት ያላቸው ናቸው ተብለው በተለዩ ሃብቶች ላይ ኢንቨስት ይደረጋል።

፫/ የካሳ ፈንዱን ሃብቶች ኢንቨስት በማድረግ የተገኙ ሁሉም ገቢዎች፣ ወለዶች፣ የትርፍ ድርሻዎች እና ሌሎች ገቢዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ስር በተቀመጠው የኢንቨስትመንት ፖሊሲ መሠረት ተመልሰው ኢንቨስት መደረግ አለባቸው።

፬/ የፈንዱን ሀብት ስብጥር፣ ብዝሃነትን እና የሀብት ምደባን በተመለከተ ባለሥልጣኑ በቦርዱ እያጸደቀ ይወስናል።

፭/ በኢንቨስትመንት ፖሊሲው ላይ የሚደረግ ጉልህ ለውጥ በቅድሚያ በቦርዱ መጽደቅ አለበት።

Draft

ክፍል ሦስት

መነሻ መዋጮ፣ መዋጮ በወቅቱ ባለመከፈል የሚጣል ቅጣት፣ በፈንዱ ውስጥ መኖር ያለበት ዝቅተኛው የገንዘብ መጠን እና ሊጣሉ ስለሚችሉ ክፍያዎች

፮. የመነሻ ካፒታል እና መዋጮ

፩/ መንግሥት ለፈንዱ የመነሻ ካፒታል ብር [xxxxxxx] ይመድባል።

፪/ ሁሉም ፈቃድ ያላቸው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ እና የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያዎች ባለሥልጣኑ በመመሪያ በሚወስነው መሠረት የመነሻ እና ዓመታዊ መዋጮ ለፈንዱ መክፈል አለባቸው።

፯. መዋጮን ባለመክፈል የሚጣል ቅጣት

፩/ በዚህ ደንብ ወይም በአዋጁ መሠረት ለፈንዱ የሚከፈልን የመነሻ መዋጮ፣ ዓመታዊ መዋጮ ወይም ማንኛውንም የሚጣሉ ክፍያዎች በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ያልከፈለ ፈቃድ ያለው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ አስተዳደራዊ ቅጣት ይጣልበታል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ስለሚጣሉ አስተዳደራዊ ቅጣቶች ዝርዝር ሁኔታ ባለሥልጣኑ መመሪያ ያወጣል።

፰. የፈንዱ ዝቅተኛ የገንዘብ መጠን

፩/ በማንኛውም ጊዜ በፈንዱ ውስጥ ሊኖር የሚገባው ዝቅተኛ የገንዘብ መጠን ብር [xxxxxxx] ነው።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ባለሥልጣኑ የገበያ ለውጦችን፣ መዋቅራዊ የአደጋ ስጋቶችን ወይም አኀዛዊ ግምገማዎችን መሠረት በማድረግ በቦርዱ ሲፈቀድ ዝቅተኛውን የገንዘብ መጠን ሊያሻሽል ይችላል።

፱. የፈንዱ ገንዘብ ከተደነገገው ዝቅተኛ የገንዘብ መጠን በታች በሚሆንበት ጊዜ የሚወሰዱ እርምጃዎች

በማንኛውም ጊዜ የፈንዱ የገንዘብ መጠን በዚህ ደንብ አንቀጽ ፰ ንዑስ-አንቀጽ ፩ ከተቀመጠው ዝቅተኛ የገንዘብ መጠን በታች ሆኖ ሲገኝ ይህ ጉድለት ከሚከተሉት መንገዶች በአንዱ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑትን በማጣመር ሊሸፈን ይችላል፡-

> **ሀ.** በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲ መሠረት በካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ፣ በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ወይም በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ላይ በሚጣል ክፍያ፣
>
> **ለ.** መንግስት የተከሰተው ጉድለት በካፒታል ገበያው ላይ መዋቅራዊ ስጋት የፈጠረ መሆኑን ሲያምን የሚሰጠው የመታደጊያ የገንዘብ ድጋፍ ወይም፣
>
> **ሐ.** በባለሥልጣኑ አማካኝነት በካፒታል ገበያ ግብይቶች ላይ በሚጣል ልዩ ክፍያ ሊሸፈን ይችላል።

፲. የፈንዱን ግዴታዎች ለማሟላት የሚጣሉ ክፍያዎች

፩/ ፈንዱ ያለው ሃብት ካለበት እዳ ባነሰ ጊዜ፡-

> **ሀ.** የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያዎች ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ለፈንዱ በሚያደርጉት ዓመታዊ መዋጮ መጠን ልክ ጉድለቱን እንዲሸፍኑ በማድረግ፣ ወይም

ለ. የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያዎች ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ለፈንዱ የሚያደርጉትን ዓመታዊ መዋጮ አስቀድመው እንዲከፍሉ በማድረግ ጉድለቱ ሊሸፈን ይችላል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(ለ) መሠረት በቅድሚያ የተከፈለ ዓመታዊ መዋጮ ወደፊት ከሚከፈሉ ዓመታዊ መዋጮዎች ላይ ተቀናሽ ተደርጎ የሚታሰብ ይሆናል።

<u>ክፍል አራት</u>

<u>የሙብት ጥያቄ ያልቀረበባቸው የተሰበሰቡ የትርፍ ድርሻዎች</u>

<u>፲፩. የሙብት ጥያቄ ያልቀረበባቸውን የትርፍ ድርሻዎችን መሰብሰብና ማስተዳደር</u>

፩/ ሕጋዊ ተጠቃሚዎች እስከሚጠይቁ ድረስ ባለሥልጣኑ ሁሉንም የሙብት ጥያቄ ያልቀረበባቸውን የትርፍ ድርሻዎችን ከሕዝብ ኩባንያዎች ይሰበስባል፣ ይይዛል እንዲሁም ያስተዳድራል።

፪/ የሕዝብ ኩባንያዎች በሕግ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የሙብት ጥያቄ ያልቀረበባቸውን የትርፍ ድርሻዎችን ወደ ፈንዱ ማስተላለፍ አለባቸው።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ከሚደረገው የትርፍ ድርሻ ማስተላለፍ ጋር ተያይዞ፣ የሕዝብ ኩባንያዎች የሚከተሉትን ዝርዝር መረጃዎች የያዘ ሪፖርት ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለባቸው፡-

ሀ) የሙብት ጥያቄ ያላቀረቡ የትርፍ ድርሻ ተጠቃሚዎችን ሙሉ ዝርዝር፤

ለ) ለእያንዳንዱ ተጠቃሚ ሊከፈል የሚገባውን የገንዘብ መጠን፤

ሐ) የተጠቃሚውን የመጨረሻ የታወቀ አድራሻ እና

መ) የሙብት ጥያቄ ያልቀረበባቸው የትርፍ ድርሻዎችን በተመለከተ ባለሥልጣኑ የሚጠይቀውን ሌላ ማናቸውንም መረጃ።

፬/ ባለሥልጣኑ ፡-

ሀ) የሙብት ጥያቄ ያልቀረበባቸው የትርፍ ድርሻዎች ወደ ፈንዱ የሚተላለፉበትን ዝርዝር ሥርዓት እና የጊዜ ገደብ፤

ለ) ከሕዝብ ኩባንያዎች የሚቀርቡ የሪፖርት ይዘቶችን፤

ሐ) የተሰበሰቡ የሙብት ጥያቄ ያልቀረበባቸው የትርፍ ድርሻዎች ተጠቃሚዎች ሲመጡ ለማጣራትና ለመክፈል መከተል የሚገባውን ሥርዓት፤ እና

መ/ የተሰበሰቡ የሙብት ጥያቄ ያልቀረበባቸው የትርፍ ድርሻዎች ተጠቃሚዎች ሲመጡ ከሚከፈሉበት ሁኔታ ጋር የተያያዙ ማናቸውንም ሌሎች ጉዳዮች በተመለከተ መመሪያ ያወጣል።

Draft

ክፍል አምስት

ከፈንዱ የሚጠየቁ የካሳ ጥያቄዎች

፲፪. ከፈንዱ ላይ የክፍያ ይገባኛል ጥያቄዎች ስለሚቀርቡበት ሁኔታ

፩. ከፈንዱ ክፍያ እንዲፈጸምለት ጥያቄ የሚያቀርብ ኢንቨስተር፣ ፡-

ሀ. የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪው ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው ወይም በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ የውል ግዴታውን ባለመወጣቱ ምክንያት የገንዘብ ኪሣራ የደረሰበት ፣ ወይም

ለ. የሙብት ጥያቄ ካልቀረበባቸው የተሰበሰቡ የትርፍ ድርሻዎች ላይ ክፍያ እንዲፈጸምለት የሚጠይቅ መሆን አለበት

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ ፩ መሠረት የሚቀርብ የክፍያ ይገባኛል ጥያቄ በራሱ በኢንቨስተሩ ወይም በሕጋዊ ተወካዩ አማካኝነት ለባለሥልጣኑ መቅረብ ይኖርበታል።

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ ፩(ሀ) መሠረት ለሚቀርብ የክፍያ ይገባኛል ጥያቄ የክፍያ ጥያቄውን የሚያቀርበው ሰው ቀደም ሲል ለካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪው ወይም ለሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው ወይም በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ጥያቄውን አቅርቦ እንደነበርና ተቋሙ ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆኑን፣ አለመቻሉን ወይም ቸል ማለቱን የሚያሳይ ማስረጃ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይኖርበታል።

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ ፩(ለ) መሠረት ለሚቀርብ የክፍያ ይገባኛል ጥያቄ የክፍያ ጥያቄ አቅራቢው የሰነደ ሙዓለ ንዋዩ ባለቤት መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እና የትርፍ ድርሻ የሙብት ጥይቄውን ሳያቀርብ የቆየበትን ምክንያት ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት።

፭. ከፈንዱ የሚጠየቅ ማንኛውም የክፍያ ይገባኛል ጥያቄ ባለሥልጣኑ በሚያዘጋጀው ቅጽ መቅረብ ያለበት ሲሆን ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የኢንቨስተሩን የክፍያ ይገባኛል ጥያቄ የሚያረጋግጡ ትክክለኛ ማስረጃዎችንና መረጃዎችን የያዘ መሆን ይኖርበታል።

፲፫. የክፍያ ይገባኛል ጥያቄ ተቀባይነት

የቀረበው የክፍያ ይገባኛል ጥያቄ ተቀባይነት የሚኖረው የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ ነው፡-

፩. የቀረበው የሙብት ጥያቄ በሕግ አግባብ ቀሪ ያልሆነ ሲሆን፤

፪. በካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪው ወይም በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው ወይም በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያው እና በኢንቨስተሩ መካከል በማንኛውም ሌላ መንገድ መፍትሔ ያላገኘ ወይም ክፍያ ያልተፈጸመለት ሲሆን፤ እና

፫. በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው የሚመራ ሌላ የካሳ ክፍያ ሥርዓትን ጨምሮ በሌላ ማንኛውም ሥርዓት ወይም ፖሊሲ መፍትሔ ያላገኘ ሲሆን የካሳ ጥያቄው ተቀባይነት ያገኛል።

፲፬. አገልግሎት ሰጪው ግዴታውን ባለመወጣቱ የሚወጣ ማስታወቂያ እና የካሳ ጥያቄ ማቅረቢያ የጊዜ ገደብ

፩. የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ወይም በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ፈቃዱ በባለሥልጣኑ በመታገዱ ወይም በመሰረዙ ምክንያት ለኢንቨስተሮች ያለበትን የውል ግዴታ መወጣት

Draft

ካልቻለ፣ ባለሥልጣኑ መታገዱን ወይም መሰረዙን ገልጾ ኢንቨስተሮች የካሳ ጥያቄያቸውን በስድስት ወራት ውስጥ እንዲያቀርቡ ጥሪ ማድረግ አለበት።

፪. በዚህ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚወጣው ጥሪ በአማርኛ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች ሆኖ፣ በመላው አገሪቱ በሚሰራጩ ቢያንስ ሁለት ጋዜጦች ላይ መታተም አለበት።

<u>፲፫. የካሳ ጥያቄ ማቅረቢያ የይርጋ ጊዜ እና መብትን ስለመተው</u>

፩. የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ወይም በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ የውል ግዴታውን መወጣት አለመቻሉን ኢንቨስተሩ ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በስድስት ወራት ውስጥ የካሳ ጥያቄው ለባለሥልጣኑ መቅረብ አለበት።

፪. በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ የካሳ ጥያቄውን ያላቀረበ ኢንቨስተር፣ የካሳ ጥያቄ የማቅረብ መብቱን እንደተወ ይቆጠራል።

፫. ኢንቨስተሩ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጥያቄውን ማቅረብ ያልቻለበትን በቂ ምክንያት ካሳየ፣ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውጭ የካሳ ጥያቄው እንዲቀርብ ሊፈቅድ ይችላል።

<u>ክፍል ስድስት</u>

<u>ከፈንዱ ካሳ የማይከፈላቸው ኢንቨስተሮች እና የካሳ ክፍያ ማስተካከያ</u>

<u>፲፬. ከፈንዱ ካሳ የማይከፈላቸው ኢንቨስተሮች</u>

የሚከተሉት ኢንቨስተሮች በፈንዱ ከሚሰጠው የካሳ ሽፋን ውጭ ይሆናሉ፡-

ሀ/ እንደ ባንክ፣ ኢንሹራንስ ኩባንያ፣ የቁጠባ እና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበራት እና ማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት ያሉ የፋይናንስ ተቋማት፤

ለ/ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንዶች፤

ሐ/ የጡረታ ክፍያ ፈንዶች፤

መ/ ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ ድርጅቶች፤

ሠ/ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች፤

ረ/ ባለሥልጣኑ በሚሰጠው ትርጓሜ መሠረት የአገር ውስጥም ሆኑ የውጭ አገር ተቋማዊ እና ብቁ ኢንቨስተሮች፤

ሰ/ በክራውድፈንዲንግ በኩል በወጡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ላይ ኢንቨስት ያደረጉ ኢንቨስተሮች፤

ሸ/ የፌዴራል እና የክልል መንግሥታት እንዲሁም በስራቸው ያሉ መስተዳድሮቻቸው እና ተያያዥነት ያላቸው አካላት፤

ቀ/ ካሳ የመክፈል ኃላፊነት ካለበት የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ጋር ግንኙነት ያለው ማንኛውም ሰው፤ ይህም የሚከተሉትን ያካትታል፡-

፩) ካሳ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች፤

Draft

፪) ካሳ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ካፒታል ውስጥ ፭ በመቶ ወይም ከዚያ በላይ ድርሻ ያላቸው ሰዎች፤

፫) ካሳ የመክፈል ኃላፊነት ላለበት የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ የሂሳብ ምርመራ የሚያከናውኑ የውጭ ኦዲተሮች፤

በ/ በዚህ አንቀጽ በፊደል ተራ (ቀ) ሥር የተጠቀሱት ሰዎች እስከ ሦስተኛ ደረጃ የሚቆጠሩ ዘመዶች፤

ተ/ ለካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪው ተጠያቂነት ማንኛውም ዓይነት ኃላፊነት ያለባቸው ኢንቨስተሮች፤ እና

ቸ/ የውጭ አገር መንግሥታት እና ተያያዥ ተቋማት።

፲፯. <u>የካሳ ክፍያ ማስተካከያ</u>

፩/ ባለሥልጣኑ በኮሚቴው ምክረሐሳብ እና በሌሎች ግምት ውስጥ መግባት በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ በመመሥረት ከፍተኛ የካሳ ክፍያ መጠንን ሊያስተካክል ይችላል።

፪/ ባለሥልጣኑ በሚከተሉት ሁኔታዎች ከፍተኛ የክፍያ መጠንን ለማስተካከል ወይም ለመቀነስ ሊወስን ይችላል፡-

ሀ) ሌሎች በሒደት ያሉ የካሳ ጥያቄዎች ብዛት ላይ ወይም የኢንቨስተሩ የተጣራ የካሳ ጥያቄ ትክክለኛ መጠን ላይ እርግጠኛ ለመሆን ሳይቻል በመቅረቱ ምክኒያት ሙሉ ክፍያ መፈጸም ተገቢ እንዳልሆነ ባለሥልጣኑ ሲያምን፤

ለ) የክፍያ ይገባኛል ጥያቄ አቅራቢው ኢንቨስተር ለደረሰበት ኪሳራ የራሱ አስተዋጽኦ እንዳለበት ባለሥልጣኑ ሲያምን፤

ሐ) ኢንቨስተሩ የካሳ ጥያቄውን በከፊል ከሦስተኛ ወገን ወይም ከሌላ የካሳ ፈንድ የማግኘት ዕድል እንዳለው ሲታመን፤

፫. ኢንቨስተሩ ለካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪው መክፈል ያለበት ዕዳ ሲኖር የሚከፈለው ካሳ በዚያ ዕዳ መጠን ተቀናሽ ይደረጋል።

<u>ክፍል ሰባት</u>

<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

፲፰. <u>ለጠቋሚዎች የሚከፈል ሽልማት ፖሊሲ</u>

ባለሥልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ <u>፩፻፰</u> (፬) ላይ በተገለፀው አግባብ ጥቆማ ለሚሰጡ ሰዎች ሽልማት ስለመስጠት የተደነገገውን ለማስፈጸም፡-

ሀ. የፈንዱን ገንዘብ ለማስመለስ የሚያስችል አዲስ እና ወቅታዊ መረጃ የሚቀርብበትን ሥነ-ሥርዓት፤

ለ. ሽልማት የማግኘት መብት የሚኖራቸው ሰዎች ሊያሟሏቸው የሚገቡ መመዘኛዎችን፤

ሐ. በአዋጁ በተቀመጡት ገደቦች እና ሁኔታዎች መሠረት ሽልማቶችን ለማስላት እና ለመክፈል የሚያስችል የአሠራር ሥርዓትን፤ እና

መ. የፈንዱ ሀብት የሆነን ገንዘብ ለማስመለስ የሚያስችል መረጃ ለሰጡ ጠቋሚዎች የሚደረግ የጥበቃ ሥርዓትን በተመለከተ መመሪያ ያወጣል።

፲፱. <u>መዝገቦች እና ሪፖርቶች</u>

Draft

፩/ ባለሥልጣኑ የፈንዱን የገንዘብ እንቅስቃሴዎች የሚያሳዩ እና የሚያብራሩ እንዲሁም በማንኛውም ጊዜ የፈንዱን ትክክለኛ የፋይናንስ አቋም በበቂ ሁኔታ የሚገልጹ መዛግብትን መያዝ አለበት፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የተገለጹትን መዛግብት ለዐሥር (፲) ዓመታት ጠብቆ ማቆየት አለበት፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ የፋይናንስ ዓመቱ በተጠናቀቀ በሦስት (፫) ወራት ጊዜ ውስጥ ዓመታዊ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡

፬/ ዓመታዊ ሪፖርቱ ከሌሎች ጉዳዮች በተጨማሪ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፡-

ሀ) በዓመቱ ውስጥ በፈንዱ ላይ የታዩ ለውጦችን የሚያሳይ መግለጫ እና በዓመቱ መጨረሻ ላይ የፈንዱን ሀብትና ዕዳ የሚያሳይ መግለጫ፤

ለ) በዓመቱ ውስጥ ወደ ፈንዱ የገቡ እና ከፈንዱ ወጪ የተደረጉ ማናቸውንም ክፍያዎች የሚያሳይ መግለጫ፤ እና

ሐ) በቦርዱ በጸደቁ የውጭ ኦዲተሮች የተዘጋጀ የፈንዱ የሒሳብ ኦዲት ሪፖርት፡፡

፭/ ባለሥልጣኑ ፈንዱን በማስተዳደር ሂደት ውስጥ የሚያጋጥሙ ጉልህ ክስተቶችን ለቦርዱ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

፳. *መመሪያ የማውጣት ሥልጣን*

ባለሥልጣኑ ይህንን ደንብ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

፳፩. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ከዚህ ደንብ ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ ደንብ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

፳፪. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ፤

---- ቀን ----- ፪ሺ -- ዓ.ም.

ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

Draft